የሰ/መ/ቁ. 36380

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረፈጅ አቶ አደም ንጉሴ ቀረቡ

**መልስ ሰጭ፡-** አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ እያከራከረ እያለ ይግባኝ ባይ የነበረው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረበት እለት አልቀረበም፡፡ መልስ ሰጭ የነበረው አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅም ክዶ ተከራክሯል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በማለት የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ/መ/ቁ. 60818 ላይ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡

የአሁን አመልካች የተዘጋው መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚያው መዝገብ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት መዝገቡ ይንቀሳቀስ ዘንድ ይግባኝ ባይ ያቀረበው ምክንያት በቂ ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት አሰናብቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን ለመዝጋትም ሆነ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ አይገባውም ሲል የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በሚል ክርክሩን ዘርዝሮ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በበኩሉ መዝገቡ ለቃል ክርክር ተቀጥሮ በነበረበት እለት ይግባኝ ባይ ያለመቅረቡን በመገንዘብ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ነው፣መዝገቡን መልስ ለመቀበልና የቃል ክርክር ለመስማት በሚል መቀጠር የሚፃረረው የሥነ-ሥርአት ሕግ ባለመኖሩ የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ይጽናልን ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም ሁለቱም ወገኖች በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን ክርክር ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ በመሆን የአሁን መልስ ሰጭ ደግሞ በመልስ ሰጭነት ተሰይመው በሚከራከሩበት ጉዳይ መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጥሮ የነበረው የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት እና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ ለመቀበል በሚል እንደነበረ በዚሁ እለት ፍ/ቤቱ በመዝገቡ ላይ ካሰፈረው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚሁ እለትም ግራ ቀኙ መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ጥሪ በተደረገላቸው ጊዜ ይግባኝ ባይ ሊቀርብ እንዳልቻለም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በተያዘ ቀጠሮ የቃል ክርክር ማድረግና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ መቀበል በክርክር አካሄድ ሁለቱም እራሳቸውን የቻሉ ሥርአቶች እንጂ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የክርክር ደረጃዎች አይደሉም፡፡ የሁለቱም ሥርአት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አኳኋን ከማዘዙ በፊት ግልጽ በሆነ አኳኋን መዝገቡ ለምን እንደተቀጠረ ለይቶ አለማዘዙ በጉዳዩ አመራር የተፈፀመ ስህተት ነው፡፡

በተለይም የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ከነበረው ቀጠሮ በፊት መዝገቡ ለቃል ክርክር በሚል ተቀጥሮ እያለ መልስ ሰጭ ጊዜ አጥሮኛል በማለት ባመለከቱት መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮው ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሆን ተደርጓል በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር መልስ ሰጭ ይህንኑ አላስተባበለም፡፡ ይህም ከሆነ ከየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፊት በነበረው ቀጠሮ መልስ ሰጭ ቀርቦ የቃል ክርክር ማድረግ እየቻለ ቀጠሮ አጥሮብኛል ማለቱ በተከታዩ ቀጠሮ ክርክሩን በጽሑፍ ለማቅረብ እንደፈለገ ስለሚያመለክት መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ ነበር ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተገለፀው በአንድ ቀጠሮ የቃል ክርክር እና የጽሑፍ መልስ ፣መልስ ሰጭ እንዲያቀርብ ብሎ ማዘዙ ሥነ-ሥርአታዊ ካለመሆኑም በላይ መዝገቡ ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ እንደሆነ በግልጽ ያልተመለከተ ስለሆነ ይግባኝ ባይ በቀጠሮው እለት አልቀረቡም እንኳ ቢባል ስለጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ተፈፃሚነት ያለው አይደለም፡፡

የይግባኝ ባይ በቀጠሮው የመቅረብና ያለመቅረብ ጉዳይ ፍ/ቤቱ እንደጀመረው የክርክሩ አቅጣጫ መልስ ሰጭ ላቀረበው የጽሑፍ ክርክር የበኩሉን የመልስ መልስ ለማቅረብ መቻሉ ወይንም ለማቅረብ ያለመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች መዝገቡ መታየት በጀመረበት እለት በመዝገብ መደራረብ ምክንያት በሌላ ችሎት በመጠራቱ እንጂ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ይህንኑ ጉዳይ እየተከታተልኩ ነበር የሚለው ክርክሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ የመልስ መልሱን የማቅረብ መብቱን ለማስጠበቅ እንጂ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 ጋር ሊገናኝ የሚችል አይደለም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 339 እንደተደነገገው የይግባኝ ክርክሩን ለመስማት ሊከተል ከሚችለው ሥርአት አንዱን ለይቶ መከተል ሲገባው በአንድ ጊዜ ሊፈፀሙ የማይችሉትን ሥርአቶች አቀላቅሎ እንዲፈፀም በማዘዙ ምክንያት እና ከሁለቱ ሥርአቶችም መዝገቡ የተቀጠረው መልስ ሰጭ የጽሑፍ መልሱን ለማቅረብ በሚል ነው የሚለውን ነጥብ የመዝገቡ ግልባጭ ስለሚያስረዳ መዝገቡ የተቀጠረው የቃል ክርክር ለማድረግ በሚል ነው፤ በዚሁ እለትም ይግባኝ ባይ አልቀረቡም፤መልስ ሰጭም ክዶ ተከራክሯል የሚለውን መነሻ በማድረግ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት ተዘግቷል ሲል የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሥነ- ስርአት ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 60818 የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እና የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጣቸው ትእዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ቀጠሮ በእራሴ ጉድለት ምክንያት ሳይሆን በቀጠሮ መደራረብ ነው የሚለው ክርክሩ ከቀረበው ማስረጃ አኳያ ታይቶ ተከታዩ ሥርአት (የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ) ይጠበቅለት እንደሆነ አስፈላጊው እንዲፈጸም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ